## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን
## የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት

# መልካም አስተዳደር
# ለቤተክርስቲያን አገልግሎትና ልማት

በሀገረ ስብከቱ በተዘጋጀው የሰበካ ጉባኤ ላይ ለታደሙ ተሳታፊዎች የቀረበ

አዘጋጅና አቅራቢ ፡ በድሉ አሰፋ ዓለማየሁ

ስልክ ፡ 0911 84 35 48 ኢሜል ፡ bediluak@gmail.com

የካቲት 20 ቀን 2013 ዓ፣ም
አዲስ አበባ

# የ አቀራረብ ቅደም ተከተል

1 . የዝግጅቱ ዓላማ

2 . የቤተ ክርስቲያናችን ከባቢያዊ ሁኔታ

3 . የቤተ ክርስቲያናችን አጠቃላይ ውስጣዊ ሁኔታ

4.  የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት

 4 . 1 አደረጃጀት

 4 . 2 የሀብት አስተዳደር

5 . መልካም አስተዳደር

 5. 1  ትርጉም

 5 .2 የ መልካም አስተዳደር መነሻ

 5. 3  ዓለም አቀፍ መለኪያዎች

 5. 4  የመልካም አስተዳደር ጽንሰ ሀሳብ በቅዱሳን መጻህፍት

6.  በቤተክርስቲያናችን የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች

 6 .1  በካህናት የሚነሱ

 6 .2  በምዕመናን የሚነሱ

7 . የጥያቄዎቹ (የችግሮቹ) ዋንኛ መንስኤዎች

8 . ጥያቄዎቹን እንዴት እንመልስ ?

9 . ማጠቃለያ

# 1. የዝግጅቱ ዓላማ

- የቤተክርስቲያኒቱን የመልካም አስተዳደር ጥንካሬና ክፍተት በመፈተሽ የተሻለ ሁኔታ እንዲፈጠር ማመላከት ፣
- የጉባኤው ተሳታፊዎች ስለመልካም አስተዳደር ያላቸውን ግንዛቤ የበለጠ እንዲያዳብሩ ማስቻል፣
- በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ እየተንሰራፋ የሚገኘውን የመልካም አስተዳደር ችግር ለመቅረፍ የሚደረገውን ዕንቅስቃሴ ማገዝ፣
- በየደረጃው ግልጽ የሆነ ያሰራርና የተጠያቂነት ስርዓት የሚዘረጋበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፣
- የቤተክርስቲያኒቱን መልካም ስምና ዝና ጠብቆ ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ

# 2. የቤተክርስቲያናችን ከባቢያዊ (ውጫዊ) ሁኔታ

- በዓለማችን ካለው 7.8 ቢሊዮን ህዝብ መካከል 95% ያህሉ የአንድ ወይም የሌላ ዕምነት ተከታይ ነው፣
- የአማኞች አጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ ፣ 2.38 ቢሊዮን (31.1%) ክርስቲያን ፣1.9 ቢሊዮን (24.9%) ሙስሊም፣ 1.19 ቢሊዮን (15.5%) ዕምነት የለሽ፣ 1.16 ቢሊዮን (15.1%) ሂንዱይዝም፣ 506 ሚሊዮን (6.6%) ቡዲዝም፣ 394 ሚሊዮን (5.6%) ባህላዊ ዕምነት ያላቸው ናቸው.
- የክርስትና አማኞችን በተመለከተ 1.3 ቢሊዮን ካቶሊክ፣ 900 ሚሊዮን ፕሮቴስታንት፣ 268 ሚሊዮን ኦርቶዶክስ ናቸው ፣
- በሀገራችን ደረጃ 43.5% ኦርቶዶክስ፣ 33.9% ሙስሊም፣ 19% ፕሮቴስታንት፣ 0.9% ካቶሊክ ይሆናሉ፣

## .........የቀጠለ

- ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በተገኘ መረጃ መሰረት የኦርቶዶክስ አማኞች ቁጥር በ 1994 ዓም 50.6% የነበረ ሲሆን በ 2007 ዓም ወደ 43.5% ዝቅ ብሎአል፣
- በነኝሁ ዓመታት የሙስሊሙ ቁጥር በ 1% ፣ የፕሮቴስታንት ደግሞ  በ 8.5% ከፍ ብሎአል፣
- የመረጃዎቹ ሁኔታ የሚያሳየው በውስጥ ችግሮቻችን ተተብትበን ዋንኛውን ጉዳይ ችላ ማለታችንንና ካለፉት 30 ዓመታት ወዲህ ግሎባላይዜሽን እየተስፋፋ ከቢዝነስ ዓለም በተጨማሪ በዕምነት አካባቢዎችም እየገባ በመሆኑ በፈጠረው  ጫና ችግር ውስጥ እንደገባን ያመለክታል፣

# 3 . የቤተክርስቲያናችን አጠቃላይ ውስጣዊ ሁኔታ

- ቤተክርስቲያናችን በ4ኛው ምዕት ዓመት በ 330 ዓም በሲኖዶስ ህግ መሰረት የኤጲስ ቆጶስ መንበር አግኝታ የተመሰረተችና ከስድስቱ ኦሪዬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት (የኮፕቲክ፣ የአርሜንያ፣ የሲሪያ፣ የማላንካራ፣ የኤርትራ) ታላቅዋ ቤተክርስቲያን ነች፣
- ከ 1951 ዓም ጀምሮ በራስዋ ፓትርያርክ በመመራት ላይ ትገኛለች፣
- በአደረጃጀትዋ መሰረት 55 አህጉረ ስብከት፣ 500 ወረዳ ቤተክህነት፣ 20 ሸህ የሚገመቱ አጥቢያ ቤተክርስቲያናትና ገዳማት፣ 370,000 ያህል ካህናት አላት፣
- 45 ሚሊዮን ከሚገመቱ ምዕመናን 78% ያህሉ ቢያንስ በሳምንት አንዴ ወደቤተክርስቲያናቸው እየመጡ እምነታቸውን ያራምዳሉ፣

# 4. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት

## 4.1 አደረጃጀት

- ሀገረ ስብከቱ የሸዋ ሀገረ ስብከት ይባል በነበረው ስር ቆይቶ ከ 1981 ዓም ጀምሮ ራሱን ችሎ ከ 55 ቱ አህጉረ ስብከት አንዱ በመሆን በከተማው ውስጥ የሚገኙ አድባራትንና ገዳማትን ይመራል:
- በሀገረ ስብከቱ ስር 7 (ሰባት) የክፍለ-ከተማ ጽ/ቤቶች፣ 246 አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት፣ 25,000 የሚጠጉ ካህናትና ሰራተኞች፣ 3,000,000 የሚገመቱ ምዕመናን ይገኛሉ፣
- ከምዕመናን አንጻር በአዲስ አበባ በ 1994 ዓም የነበረው የ 82% ድርሻ በ 2007ዓም ወደ 74.7% ዝቅ ብሎአል፣ ይህም 7.3% ቅናሽ ሲሆን በሌላ በኩል ሙስሊምና ፕሮቴስታንት እያንዳንዳቸው በ 4% ከፍ ብለዋል፣

# መዋቅራዊ አደረጃጀት




**በቃለ አዋዲው መሰረት ፣**

- **ሀገረ ስብከቱ በሊቀ ጳጳስ የበላይነት ዋና ስራ አስኪያጁ በዋና አስፈጻሚነት ስራውን የሚመራ ሲሆን ጽ/ቤቱ በ 13 የስራ ክፍሎች ተደራጅቶአል፣**
- **የክፍል-ከተማ ጽ/ቤቶችና እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም በተመሳሳይ የስራ ክፍሎች ተደራጅተዋል፣**
- **በተግባር ሲታይ ግን አንዳንድ የስራ ክፍሎች ያለ አንዳች ስራ ሰው ተቀምጦባቸዋል፣**
- **የቃለ አዋዲው መዋቅር በራሱ የስራ ክፍሎች ድግግሞሽ ችግር አለበት፣( ሂሳብ ክፍልና ገንዘብ ቤት፣ ስብከተ ወንጌል ክፍልና መንፈሳዊ ትምህርት ክፍል፣) በተጨማሪ የሰው ሀብት የስራ ክፍል ሳይጠቀስ ታልፎአል፣**

## 4.2 የሀብት አስተዳደር

- የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እንደምስረታ ጊዜያቸው፣ እንደምዕመኑና እንደሀብት አቅማቸው መጠን ከፍተኛ፣ መካከለኛ ፣ ዝቅተኛና ጀማሪ በመባል ተደራጅተዋል፣
- በያመቱ በአማካይ የሚንቀሳቀሰው ሀብት መጠን ባጠቃላይ የሁሉንም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ጨምሮ ብር 1,618,204,000 ሲሆን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ ከገቢያቸው 20% ለሀገረ ስብከቱ ስለሚልኩ ሀገረ ስብከቱ ባመት ብር 323,640,800 ያንቀሳቅሳል፣
- ከፍተኛ አብያተ ክርስቲያናት እስከ ብር 25,000,000፣ መካከለኛዎቹ እስከ ብር 10,000,000፣ ዝቅተኞቹ እስከ 3,000,000፣ ጀማሪዎቹ እስከ 600,000 ያንቀሳቅሳሉ፣

# 5. መልካም አስተዳደር  (Good Governance)

## 5.1 ትርጉም ፣

- ስለ መልካም አስተዳደር ለመረዳት በቅድሚያ የአስተዳደርን (Governance) ትርጉም ማወቅ ያስፈልጋል፣
- አስተዳደር (Governance) ማለት ባንድ ሀገር / ተቅዋም የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ አመራር ውስጥ ሀብትን ለልማትና ለዕድገት ለማዋል የሚያስችል የስልጣን አጠቃቀም ዘዴ ነው፣ (ዓለም ባንክ - World Bank 1992)
- አስተዳደር (Governance) የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የአስተዳደራዊ ስልጣንን በመጠቀም የሀገርን፣ የተቅዋምን፣ የህዝብን ጉዳይ በሁሉም ደረጃ ማስተዳደር ነው፣ (የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት (UNDP) 1997),
- ስለሆነም አንድን ሀገር/ተቁዋም በማስተዳደር ሂደት ውስጥ የሚሰጡ ውሳኔዎችና አፈጻጸማቸው የህዝብን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ከሆነ “ መልካም አስተዳደር“ ይባላል፣

## ……. የቀጠለ

- “ የቤተ ክርስቲያን መልካም አስተዳደር “ ሲባል የቤተ ክርስቲያኒቱን ተልዕኮ በብቃት ለማስፈጸም የሚያስችል አስተዳደራዊ ስርዓት በመዘርጋት ካህናቱን፣ ስራተኛውንና ምዕመኑን ተጠቃሚ በሚያደርግ አግባብ በግልጽነት፣ በሀላፊነትና በተጠያቂነት መንፈስ መስራት ማለት ነው፣
- በቤተክርስቲያን መልካም አስተዳደር አፈጻጸም ፣
  . ቅዱስ ሲኖዶስ (እንደበላይ አመራር)
  . ጠቅላይ ቤተ ክህነት፣ አህጉረ ስብከትና የወረዳ ቤተክህነት (እንደ አስፈጻሚ አካል)
  . ካህናት፣ ስራተኞችና ምዕመናን (እንደ ተገልጋይና ተሳታፊ) ዋንኛ ተዋናይ ሲሆኑ
  . ሌሎች ባለድርሻ አካላት (መንግስት ከማዕከል እስከ ቀበሌ) ከማህበረሰብ ተጠቃሚነት አንጻር ድርሻ አላቸው፣

## 5.2 የመልካም አስተዳደር መነሻ

- የመልካም አስተዳደር ጽንስ-ሀሳብ በስፋት ስራ ላይ የዋለው በዓለም አቀፍ የልማት ዕንቅስቃሴ ውስጥ መንግስታዊና ህዝባዊ ተቁዋሞች አስተዳደራዊ ጉዳያቸውን እንዴት ይፈጽሙ እንደነበረና ሀብታቸውን እንዴት ያስተዳደሩ እንደነበረ በተደረገ ግምገማ መነሻ ነው፣
- በተደረገውም ግምገማ የተቁዋሞቹ አሰራር ውጤታማ ያልነበረ፣ስራው ከሚፈልገው በላይ ያለበቂ ስራ በሰው ሀይል የተጣበበ፣ አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋ ያልሆነ፣
  ለብልሹ አሰራርና ምዝበራ የተጋለጠ መሆኑ ታይቶአል፣
- ስለሆነም ተቁዋሞች የሚያገለግሉትን ህዝብ ፍላጎት ለማሙዋላት፣ ያለባቸውን ሀላፊነት፣ ያሰራር ስርዓት መለኪያዎችን፣ ደካማና ብልሹ አሰራርን ለማስወገድና ለማስተካከል የሚያስችል “ የመልካም አስተዳደር ሞዴል “ አወጡ፣ ሞዴሉም በሀገራትና በቁዋሞች እንዲተገበር ድጋፍና ትብብር

## ……. የቀጠለ

- የዓለም ባንክ (World Bank) ያወጣው የመልካም አስተዳደር ስታንዳርድ ፣
  . የሀገር / የተቋዋም አስተዳደር ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ኢኮኖሚያዊ መሆን፣
  . የተጠያቂነትና ያሀላፊነት ያሰራር ስርዓት መኖር፣
  . የመረጃዎች ለህዝብ/ ለተገልጋይ በግልጽና በይፋ መገለጽ፣
  . የህግ የበላይነት መከበር፣ የሰብዓዊ መብት መረጋገጥ፣
- የእንግሊዝ ዓለም አቀፍ ልማት ድርጅት (DFID ) ስታንዳርድ፣
  . የተገልጋዩን ይሁንታ የያዘ አሰራር መኖር፣
  . በአሰራርና በአገልግሎት አሰጣጥ ግልጸኝነት መኖር፣
  . የሀላፊነትና የተጠያቂነት ስርዓት መስፈን፣
  . ብቁና ውጤታማ የሆነ ፖሊሲ፣ ደንብና መመሪያ መኖር፣
  . የህግ የበላይነት መረጋገጥ፣ የሰብዓዊ መብት መከበር፣

## 5.3 ዓለም አቀፍ መለኪያዎች (Standards)

- **ተጠያቂነት (Accountability)**
  ለሚወስኑት ውሳኔና ለሚፈጽሙት ተግባር ሀላፊ የመሆን፣
  ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ የመስጠትና የማብራራት፣

- **ግልጸኝነት (Transparancy)**
  የሚወሰኑ ውሳኔዎችንና የሚወስዱ እርምጃዎችን ለምን፣ እንዴት፣ በየትኛው የህግ ያስራር ስርዓት እንደተፈጸመ ተገልጋዩ በግልጽ እንዲያውቃቸው መረጃ መስጠት፣

- **ፈጣን ምላሽ (Responsiveness)**
  የሚስጡ አገልግሎቶች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ፣ በተገቢው የሞያ ስነምግባር መሰረት እንዲስጡ ማድረግ

## ..... የቀጠለ

- **<u>ውጤታማነትና ቀልጣፋማነት (Effectiveness & Efficiency)</u>**
  ሀብትን በአግባቡ በመጠቀም የተገልጋዩን ፍላጎት ማማላት
  ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት
  ዘላቂነት ያለው ውጤታማ ስራ መስራት
- **<u>የህግ የበላይነት (Rule of Law)</u>**
  በህግ፣ በደንብና በመመሪያ የወጡ መብቶችንና ግዴታዎችን በሁሉም ላይ በእኩልነት መፈጸም፣
- **<u>አሳታፊነት (participation)</u>**
  በሚወጣ ደንብና መመሪያ፣ በሚተላለፉ ዋና ዋና ውሳኔዎች ላይ ተጠቃሚውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማሳተፍ

## …… የቀጠለ

- **<u>ፍትሀዊነትና አካታችነት (Equitable & Inclusive)</u>**
  በህግ የተለየ ድጋፍ እንዲደረግላቸው የተደነገገላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች በህጉ መሰረት መብታቸውን ማክበር፣
  ሁሉም በተቋዋሙ/ በሀገሩ / ጉዳይ እንዲሳተፍ ማድረግ፣

- **<u>የጋራ መግባባት (Consensus)</u>**
  የተገልጋዮችን የተለያዩ ፍላጎቶች በማስታረቅና በማቻቻል ሁሉም ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣
  በመሰረታዊ ጉዳይ ላይ ጠቅላላ መግባባት ላይ መድረስ፣

## 5.4 የመልካም አስተዳደር ጽንሰ ሀሳብ በቅዱሳን መጻህፍት

- “ ከህግ ወጥተው የበደሉ በህግ ይፈረድባቸዋል፣ ያለ ህግ የበደሉ ሁሉም ያለ ህግ ይፈረድባቸዋል”
  (ሮሜ 2 12)
- “ መማለጃን አትቀበል፣ መማለጃ የዓይናማዎችን ዐይን ያሳውራልና፣ እውነተኛ ቃልንም ያጣምማል “
  (ዘፀአት 23 8)
- “ የገዥዎች ሀላፊነት ቀና ፍርድ መፍረድ ፣ ህጉን መጠበቅ ነው “ (መጽሀፈ ጥበብ 6 1-11)
- “ ወንድሞቻችን ! ህግን ለሚያስታውሱ እናገራለሁና ሰው በህይወት ባለበት ሁሉ ህግ እንዲገዛው አታውቁምን “
  (ሮሜ 7 ፣ 1)

# 6 . በቤተክርስቲያናችን የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች

## 6.1 በካህናትና በሰራተኞች የሚነሱ፣

- አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለማስፈጸም (ዝውውር፣ ዕድገት፣ ) በብዙ ሽህ ብር የሚቆጠር ገንዘብ እንድንሰጥ እንጠየቃለን፣
- መማለጃ ገንዘብ በሚሰጡ ሰዎች ምክንያት ለነሱ ለማመቻቸት ሲባል ከደንቡ ውጭ ከነበርንበት የስራ ቦታ ያለ ፈቃዳችን ወደ ሌላ ቦታ እንድንዛወር ይደረጋል፣
- አሰራሩ በጎሰኝነት፣ በዝምድና፣ በትውውቅ፣ በምልጃ የሚሰራ በመሆኑ ከዚህ ውጭ የሆንነውን እየጎዳን ነው፣
- ስራዎች በዕቅድና በፕሮግራም ስለማይመሩ ከፍተኛ የሀብት ብክነት አስከትለዋል፣
- በመንፈሳዊውም ሆነ በአካዳሚክ ትምህርትና ስልጠና በመውሰድ ራሳችንን ለበለጠ ተልዕኮ እንድናዘጋጅ አይደረግም፣
- አስተዳደራዊ መዋቅሩ የላላ በመሆኑ አገልግሎት የሚሰጠው በዘፈቀደ ነው፣ አስፈጻሚዎች ከህግና ከደንብ ውጭ የፈለጉትንና የመሰላቸውን የመስራት አስተሳሰብ አላቸው፣

## ..... የቀጠለ

- ውሳኔዎች በተገቢውና ባጭር ጊዜ ውስጥ ስለማይሰጡ ተገልጋዮች ለከፍተኛ ቅሬታና እንግልት ተዳርገዋል,

**6.2 በምዕመናን የሚነሱ፣**

- የስብከተ ወንጌል ትምህርት አስጣጡ ከሌሎች ፕሮግራሞች ጋር ተዳብሎ የሚሰጥ በመሆኑ ለዚህ ዋና ተግባር በቂ ጊዜ አይሰጠውም፣
- መንፈሳዊ አገልግሎቶች ወጥ በሆነ መንገድ አይከናወኑም፣ እንደ ምዕመኑ ዐቅምና ደረጃ እየታየ ስለሚሰጥ ለብልሹ አሰራርና ለጉቦ መንገድ ከፍቶአል፣
- የመንፈሳዊ አገልግሎት አሰጣጡ ከዓለማዊ ተግባራት ጋር የተደበላለቀ በመሆኑ የስነ ምግባርና የዲሲፕሊን ችግር አስከትሎአል፣
- በየመድረኩ የሚሰጠው አገልግሎት ከዋንኛ ተልዕኮው ውጭ በሌሎች ጉዳዮች ስለሚጣበብ የተንዛዛና የቤተ ክርስቲያኒቱን ክብር በሚያስጠብቅ ሁኔታ አይመራም፣

# 7. የጥያቄዎቹ (የችግሮቹ ) ዋንኛ መንስኤዎች

- በዕቅድና በፕሮግራም የመስራት ልምድ ያለመኖር፣
- ለደንብና ለስርዓት ተገዥ ያለመሆን፣
- የአገልግሎት አሰጣጥና የአስተዳደራዊ አሰራሮችን በግልጽ የሚያመላክት ሁሉም የተሳተፈበትና የሚያውቀው ደንብና ስርዓት ያለመኖር፣
- ካህናቱም ሆነ አስፈጻሚ አካላቱ ጉዳዮችን በገንዘብ ሀይል እናስፈጽማለን የሚል የተሳሳተ ግንዛቤና አስተሳሰብ መያዝና ማራመድ፣
- የየስራ ዘርፉ ሀላፊዎችና አስፈጻሚዎች የተሰጣቸውን ሀላፊነትና የስራ ድርሻ በአግባቡ ለመወጣት ድፍረት ማጣት፣
- ለትምህርትና አቅም ግንባታ በየደረጃው የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን፣

# 8. ጥያቄዎቹን እንዴት እንመልስ ?

- የቀረቡት ጥያቄዎችና ችግሮች የሁሉም (የተገልጋዩም የአስፈጻሚውም) ችግሮች መሆናቸውን ማመንና መቀበል፣ ለመፍትሄ አሰጣጡ ራስን ዝግጁ ማድረግ፣
- ያሰራር ስርዓቶችን በየደረጃውና በየስራ ዘርፉ ለአፈጻጸም በሚያመች ሁኔታ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ታክሎበት ባስቸኩዋይ እንዲዘጋጅና በህግ (በደንብ፣ በመመሪያ) ተደንግጎ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣
- አገልግሎቶች ሁሉ “ በወንጌል ትምህርት ማዕከልነት” እንዲፈጸሙ ማድረግ፣
- ችግሮቹን ለመፍታት የሚደረገውን የስራ ዕንቅስቃሴ ልምዱ፣ ችሎታውና ብቃቱ ባላቸው ሰዎች በዕቅድና በፕሮግራም እንዲመራ ማድረግ፣
- ዕቅዱንና አፈጻጸሙን በየጊዜው በመገምገም የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣
- ስራውን ለመደገፍ በቂ ዕውቀትና ልምድ ባላቸው ባለሞያዎች በመታገዝ መፈጸም፣
- እስከ ታችኛው ዕርከን ድረስ ያሉ አባላትን በፕሮግራሙ ማሳተፍ፣

# 9. ማጠቃለያ

በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እንዲኖር የሚጠበቀው የተጠናከረ የወንጌል አገልግሎት፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ሰላምና የመልካም አስተዳደር መስፈን እንጂ እንደ ዓለማዊው አሰራር ሀብትንና ንብረትን መዝረፍ፣ የግል ጥቅምን ማሳደድ፣ ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም፣ በተለያዩ ቡድናዊ ስሜቶች መከፋፈል፣ ተገልጋዩን ማሳዘን ሊሆን አይገባም፣

አሁን እየታየ ያለው “ መጥፎ አስተዳደር (Bad Governance) “ በቶሎ ካልተስተካከለ የቤተ ክርስቲያኒቱ ህልውና አደጋ ላይ እንደሚወድቅ ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል ፡፡

የመንግስት ፍላጎት ጠንካራ የዕምነት ተቋዋማት እንዲኖሩ እንደሆነ ስለሚገለጽ ይህን አጋጣሚ በብልሀትና በጥንቃቄ መጠቀም ይገባል፣



‹‹....የሚያገለግልም በማገልገሉ ይትጋ፣

የሚያስተምርም በማስተማሩ ይትጋ፣

የሚመክርም በመምከሩ ይትጋ.....››

(ሮሜ 12:7)

ወስብሀት ለእግዚአብሄር